# ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅስለት!

በሰሜን በደቡብ ለሃያ አምሥት አመት፤

ሲነገረው ነበር አገርህ ከእንግዲህ

ይች መንደርህ ናት።

ያንተም መታወቂያ ጎሣህ ብቻ ሳይሆን

ይህ ነው የሰጠሁህ፤

እርሳው መባልህን አንተ ኢትዮጵያዊ ነህ።

ፓለቲካም ቢሆን፣

እስከ ጠላህ ድረስ አማራ መባልን፣

ይህ ነው የምመክርህ፤

ከኔ "ወርቅ" ጎሣ ጋር

ይልቅስ ተባበር፣ ሰጥ፣ ለበጥ፣ እያልህ።

እንዲያ ካልሆነ ግን

አማራ እንደ ሆነው

በጥይቱ ምጣድ አንተም ትቆላለህ፤

በክልል በቋንቋም ትታሰራታለህ።

ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅሥለት

ለሆነው የቁም ሙት፣

ለሌላው ቀብር ሲምስ

ተራ ይደርሰዋል በኢትዮጵያ እምነት፤

ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅስለት።

ኢትዮጵያ አገሪ እራቡ በዝቶብሽ ምኑን መርዝ በላሽው፤

ጥማቱም ከፍቶብሽ ምኑን ውኃ ጠጣሽው?

አገሪ ኢትዮጵያ እኔ ከዚያ ሳድግ እንዲህም አልነበረም

እንዴትስ እንድ ልምድ ይህነን ተቀብልሽ?

ምንስ መንግሥት አቋቋምሽ?

ልጆችሽን ሁሉ በጎሣ ከፋፍሎ

ባዲስ ፍልስፍና ልክ እንደባርነት፤

ተው አወግዝሃለሁ፣ በቃ!

የሚል ቁስም በጠፋበት፣

ለአረቡ ሐብታሞች ድኃ ልጆችሽን የቸረቸረበት።

ኢትዮጵያ አገሪ ምን መንግሥት አቋቋምሽ፤

ልጆችሽን ሁሉ የሚያስወጣ ካጥርሽ።

አየሁ በዳር ደንበር በኢርትራም ጭምር፣

በሥር ቤት ሲማቅቅ የኢትዮጵያ ወታደር፤

በሐረር፣ በጅማም፣ በጎንደርም ሰፈር።

ማን አለብኝ ብሉ ደማቸውን ሲያፈስ፣

አትላኩኝ ፓርላማ ብሶቴን ለመንገር፤

መች በግሩ ቆመና መብት ለማስከበር።

ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅሥለት፤

ለሆነው የቁም ሙት፣

ለሌላው ቀብር ሲምስ

ተራ ይደርሰዋል በኢትዮጵያ እምነት፣

ተው አትከልክሉኝ እኔ ላልቅስለት።

አትላኩኝ ፓርላማም ብሶቴን ለመንገር፤

መች በግሩ ቆመና መብት ለማስከበር።

© ለምለም ፀጋው፣ **July 13, 2016**

በሰሜን፣ በመካከልና በደቡብ ኢትዮጵያ የዚግነት መብታቸው ተገፎ ለሚገደሉና ለታሰሩ ሁሉ የሚጮህ ድምጽ